# የክርስትና እምነቶች(4)

## ጥናት አንድ (መዝሙር 19)

የጥናቱ ዓላማ፡- እግዚአብሄር ለፍጥረቱ ራሱን በምን በምን መንገዶች እንደገለጠ ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፡- የቅርብ ጓደኛህን አስብና በምን መንገድ ይህንን ያህል የጠለቀ መተዋወቅና መቀራረብ እንደቻላችሁ አስረዳ።

1. መዝሙር 19፥1-6 ትን በማንበብ መዝሙረኛው የማይታየውን እግዚአብሄርን በምን ዓይነት መንገድ እንድናየው ነው የሚነግረን?
2. መዝሙረኛው ዓለምን ልክ ጥሩ ስዕልን እንደምናይ ነው እያየ ያለው።የዚህ ዓይነቱ አመለካከት በምን መንገድ የእግዚአብሄርን ክብር እንድናደንቅ ይረዳናል?
3. በዚህ ክፍል መዝሙረኛው ፍጥረት ሁሉ በራሱ ቋንቋና ስለ እግዚአብሄር እንደሚናገር ያሳያል። የሰው ልጅ ከፍጥረት ስለፈጣሪው ምን መረዳት ይችላል ትላለህ?
4. ስለ እግዚአብሄር በፍጥረት አማካኝነት ልናውቅ የማንችላቸው ነገሮችስ ምንድናቸው?
5. ከቁጥር 4-6 ባለው ክፍል ፀሐይ በተለየ መንገድ ተጠቅሶ ይገኛል። የእግዚአብሄርን ክብር በምን መንገድ ነው በተለይ በፀሐይ ተገልጦ የምናየው?
6. ከተፈጥሮ በሙሉ ስለእግዚአብሄር ክብር በይበልጥ እንድታውቅ የረዳህ የትኛው ነው ትላለህ? በምን መንገድ?
7. መዝሙር 19፥7-14 ስናነብ መዝሙረኛው ትኩረቱን በተፈጥሮ ከሚገለፀው እግዚአብሄር በህግጋቱ ወደመገለጡ ይዞራል። የእግዚአብሄርን ህግጋት ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ቃላት በዚህ ክፍል ምን ምንድናቸው?
8. መመዝሙረኛው አባባል የእግዚአብሄርን ህግ ማወቅ ጥቅሙ ምንድነው ይላል? አንተንስ በህይወትህ በምን መንገድ ጠቅሞሃል?
9. ከፍጥረት ልንማራቸው የማንችላቸው ነገር ግን ከህግጋቱ ልንማራቸው የምንችላቸው ነገሮች የትኛዎቹ ናቸው?
10. ዳዊት ስለፍጥረቱና ህግጋቱ አሰላስሎ ወደራሱ ህይወት ዘወር በማለት እንዲመለከት የተገደደበት ምክንያት ምንድነው ትላለህ?
11. እግዚአብሄር ራሱን መግለጥ የሚወድ አምላክ ነው። እርሱን በበለጠ እንድታውቅ ካስፈለገ ማድረግ የሚኖርብህ ነገር ምን ይመስልሃል?

# <u>ጥናት ሁለት(ኢሳያስ 40፥9-31)</u>

<u>የጥናቱ ዓላማ፡-</u> የእግዚአብሄርን መለኮታዊ ሃይል በማወቅ መበረታታትና መጽናናት እንዳለ ለማሳየት።

<u>የጥናት መክፈቻ፡-</u> የተለያዩ ሰዎች የእግዚአብሄርን ማንነትና ምን እንደሚመስል የሚሰጡትን ሃሳብ ሰምተህ ታውቃለህ?

1. ኢሳ 49፥9-14 ስናነብ በብሉይ ኪዳን የነበሩት ሰዎች ስለእግዚአብሄር የሚያውቁትን ለመናገር ፍላጎት እንደነበራቸው እንረዳለን። በቁ 9-11 እግዚአብሄርን በተመለከተ የምናነበው መልካም ዜና ምንድነው?
2. ኢሳያስ በቁጥር 12-14 የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች በምን መንገድ በእግዚአብሄር እንድንታመን ይረዱናል ትላለህ?
3. ቁጥር 15-24 በማንበብ በምርኮ በባቢሎን ለነበሩ የእስራኤል ልጆች ምን ዓይነት መጽናናት ይሆናል ብለህ ትገምታለህ? ለምን?
4. እግዚአብሄር በመንግስታትና በነገስታት ሁሉ ላይ ሃይል እንዳለው ማወቅህ ለአንተ በምን መንገድ መፅናናት ይሆንልሃል?
5. ሃብታሞችም ሆነ ድሆች የሚታመኑባቸው አማልክት (18-24) ከእግዚአብሄር ሃይል ጋራ ሲነጻጸሩ እንዴት ሆነው ታያቸዋለህ?
6. አሁንስ በእኛ ዘመን ምን ምን ዓይነት ነገሮች አማልክት ሆነው ሲመለኩ ታስተውላለህ?
7. ሕያውንና እውነተኛውን እግዚአብሄርን ከማወቅ ይልቅ ሰዎች በዙጊዜ ጣዖትን ለመከተል የሚመርጡት ለምን ይመስልሃል?
8. ቁጥር 25-31 በማንበብ አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሄር ፍጥረቱን በሩቅ ሆኖ የሚመለከት እንጂ ከፍጥረቱ ጋራ የማይገናኝ አድርገው ይናገራሉ። ቁ 26 ስለዚህ ምን ያስተምራል?
9. በቁጥር 27 ላይ ይሁዳ በሕይወትዋ የሚከናወነው ሁሉ ከእግዚአብሄር የተሰወረ እንደሆነ ትናገራለች። አንተስ በፈተና ውስጥ ስትሆን እግዚአብሄር የረሳህ የመሰለህ ሰዓት አለ ወይ?
10. ቁጥር 28-31 ኢሳያስ እግዚአብሄር የረሳን ለሚመስለን ሰዓቶች የመሰጠን ተስፋ ምንድነው?
11. ደክመህ በነበርክበት ሰዓት እግዚአብሄር ሃይልህን ያደሰልህና እንደንስር በክንፍ እንድትበር የረዳህን ጊዜ ታስታውሳለህ? እስቲ ለወገኖች መስክረው።

## ጥናት ሶስት (ዮሃንስ 1፥1-18)

<u>የጥናቱ ዓላማ</u>፡- እግዚአብሄር በልጁ በኩል ወደእኛ ስለመጣና ልጆቹ ስላደረገን ምስጋናን ለማብዛት።

<u>የጥናት መክፈቻ</u>፡- የእግዚአብሄር ልጅ መሆንህን ለሰዎች ነግረህ ታውቃለህ? ምን ዓይነት ምላሽ አገኘህ?

1. ዮሃንስ 1፥1-18 ስናነብ "ቃል" ስለሚለው የምንማቻቸው ጠቃሚ እውነቶች ምንድናቸው?
2. ዮሃንስ ስለ "ቃል" ካሰፈረው ሃሳብ ልናያቸው የምንችላቸው እውነቶች ምንድናቸው?
3. ከቁጥር 1-9 ዮሃንስ ኢየሱስን "ቃል" "ሕይወት" ና "ብርሃን" በማለት ይገልጸዋል። እነዚህ ሥዕሎች ስለኢየሱስ ማንነት ምን ያስረዱናል?
4. ቁጥር 6-8, 15 በማንበብ ዮሃንስን በአሁኑ ዘመን በፍርድ ቤት ከሚቆሙት ምስክሮች ጋራ የስራውን ተመሳሳይነት እንዴት ማነፃፀር ይቻላል?
5. በቁጥር 9-11 መሰረት ብዙ ሰዎች ስለኢየሱስ ያልተረዱት ትልቅ ነገር ምን ነበረ ትላለህ?
6. በቁጥር 12-13 መሰረት በክርስቶስ ኢየሱስ ማመናችን የሚያስገኝልን ምንድነው?
7. የክርስቶስ ሥጋ መልበስ በቁጥር 14ና18 መሰረት እግዜአብሄርን ማወቅን ያቀለለልን በምን መንገድ ይመስልሃል?
8. ፀሐፊው ዮሃንስ ከኢየሱስ ጋራ አብሮ የመኖሩን ልምምድ በምን መንገድ ነው የሚገልፀው? (ቁ 14, 16-18)
9. ዮሃንስ በቁጥር 16 በፀጋ ላይ ፀጋ (በበረከት ላይ በረከት) ተቀበልን ይላል። አንተስ በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሄር ጋራ ባለህ ግንኙነት ምን በረከት ተቀብለሃል?
10. በጌታ በየሱስ አገልግሎት ፀጋ ብቻ ሳይሆን እውነትም ጭምር ነው የመጣው። ለምንድነው እነዚህ ሁለቱ መለያየት የማይችሉት? (ቁ 14, 17)
11. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለኢየሱስ ለመናገር የሚገፋፋህ ክፍል የትኛው ነው?

## ጥናት አራት (ዮሃንስ 14፥15-27)

የጥናቱ ዓላማ፡- የሚያጽናናን የሚመክረንና የሚመራንን መንፈስ ቅዱስ በማዳመጥ ሕይወት እንድናድግ ለማበረታታት።

የጥናት መክፈቻ፡- እግዚአብሄር ለመኖሩ ጥያቄ የሆነብህ ጊዜ የለም? ከሆነስ እንዴት ተወጣህው?

1. ዮሃንስ 14፥15-27 ስናነብ ኢየሱስ ትቶአቸው ስለሚሄድ በፍርሃት ተይዘው ይታያሉ። ኢየሱስ ምን በማለት ነው የሚያጽናናቸው? (ቁ 15-18)
2. አፅናኝና የእውነት መንፈስ የሚለው የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ(ቁ 16-17) በውስጣችን ስለሚኖረው መንፈስ ምንን ያስረዳናል?
3. እግዚአብሄር እንደተወን የሚመስለን ስሜት ሲሰማን በቁ 16-17 የመንፈስ ቅዱስ በቋሚነት በውስጣችን እንደሚኖር ቃል መግባቱ በምን ዓይነት ያጽናናናል?
4. በቁጥር 18 ኢየሱስ አባት እንደሌላቸው ልጆች እንደማይተወን ቃል ገብቶልናል።ይህ ቃልኪዳን ለየቀኑ ኑሮአችን እንድንታመነው እንጅ እንዳንጨነቅ እንዴት ይረዳናል?
5. በቁጥር 21-24 መሰረት እኛ ፍቅራችንን የምናሳየው እንዴት ነው? እርሱስ ለእኛ ፍቅሩን የሚገልጽበት መንገድ እንዴት ነው?
6. ኢየሱስ በመከራ ውስጥ እኝኚን ሰላምን ቃል ገብቶልናል(27)። የትኞቹ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ናቸው ለአማኞች ሰላምን የሚያመጡት? እነዚህን አገልግሎቶቹን በህይወትህ ተለማምደሃቸው ታውቃለህ ወይ?
7. አለም በምትሰጠውና ኢየሱስ በሚሰጠው ሰላም መሃል ስላለው ልዩነት ከዚህ ክፍል ውስጥ ምን ታያለህ?
8. በዚህ በምናጠናው ክፍል ስለአብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ግንኙነት ምን ትመለከታለህ?
9. መንባብ ክፍሉ ውስጥ ኢየሱስ በመደጋገም ህግጋቱን እንድንጠብቅ ይነግረናል።(ቁ 15-16, 21, 23) ጌታን ለማወቅ ያለህ ፍላጎት ለእርሱ ለመታዘዝ በምን መንገድ ሲገፋፋህ ወይም ሲያበረታታህ ታያለህ?

# ጥናት አምስት (ዘፍጥረት 1፥24-2፥25)

<u>የጥናቱ ዓላማ</u>፡- የሰው ልጅ ምንነቱና ክብሩ በእግዚአብሄር መልክ መፈጠሩ ብቻ እንደሆነ ለመማር።

<u>የጥናት መክፈቻ</u>፡- ስለራስህ ስታስብ ደስ የምትሰኝበት ወይም የምትከራበት ሃሳብ ምንድነው?

1. ዘፍጥረት 1፥24-2፥25 በማንበብ የሰው ልጅ የተፈጠረው በስድስተኛው ማለትም እንስሳትም በተፈጠሩበት ቀን ነው። እግዚአብሄር የሰውን አፈጣጠር ልዩ ደረገባቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?
2. በቁጥር 1፥26-30 ና 2፥4-25 ያሉትን ስለሰው አፈጣጠር የተሰጡትን ክፍሎች አነፃፅርና እያንዳንዳቸው ያተኮሩባቸውን ሃሳቦች ግለጽ።
3. ከላይ ያነፃፀርናቸውን በአንድነት ስንመለከት ስለራሳችንና ስለማንነታችን ምን ያስተምሩናል?
4. 2፥15-18 በአዳምና በእግዚአብሄር መሃል የነበረውን ግንኙነት እንዴት ትመለከተዋለህ?
5. አዳምን በዙሪያው ከነበሩት እንስሳት ጋራ ብቻ ቢሆንና ከእግዚአብሄር ጋራ የነበረው ህብረትና ግንኙነት ባይኖር ህይወቱ በምን መንገድ የተለየ የሚሆን ይመስልሃል?
6. ዛሬስ በአንተ ህይወት እግዚአብሄርን ማወቅህ በአኗኗርህና ስለራስህ በሚኖርህ አመለካከት ላይ ምን አስተዋጾ እንዳለው ታስባለህ?
7. ክፉንና ደጉን ከምታስታውቀው ዛፍ በስተቀር አዳም በአትክልቱ ስፍራ ሙሉ ነጻነት እንደነበረው ይታያል(ዘፍ 2፥15-17)። ይህን በማድረጉ እግዚአብሄር ለአዳምና ለሄዋን ለማስተማር የፈለገው አንድ እውነት ምን ይመስልሃል?
8. አዳም ለእንስሳቱ ስም ሲሰይም የብቸኝነት ስሜቱ ታየው(ቁ 18-25)። ከዚህ ክፍል ለአዳምና ለሄዋን አንዱ ከሌላው ጋራ ለሚኖራቸው ግንኙነት እግዚአብሄር የነበረው እቅድ ምን ይመስልሃል?
9. ሔዋን በምን መንገድ ይመስልሃል ለአዳም በአካባቢው ያሉት ፍጥረቶች ሁሉ ሊሞሉት የማይችሉትን ባዶነት የምትሞላለት?
10. እግዚአብሄር ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም(ቁ 18) አለ። ከራስህ ልምድ ብቸኛ መሆን ምን ችግር አለበት ትላለህ?
11. ዛሬ የተማርከው ክፍል ስለራስህ ስለሚኖርህ አመለካከት የተከበርክ ፍጥረት ስለመሆንህ እንድትረዳ በምን መንገድ አስተዋጾ ያደርጋል?

# ጥናት ስድስት (ዘፍጥረት 3፥1-24)

የጥናቱ ዓላማ፥- ሃጥያት በሰው ልጅ ላይ ያስከተለውን ነገር ለመመልከትና ከዚህም ሁኔታ ውስጥ ለማውጣት የእግዚአብሄር እጅ እንደሚያስፈልግ ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፥- እግዚአብሄር እውነት ሰዎችን የሚወድ ከሆነ ለምን ይህ ሁሉ መከራ በሰዎች ላይ ሲደርስ ዝም ብሎ ያያል ብለው ሰዎች ሲጠይወቁ ሰምተህ ታውቃለህ ወይ?

1. ዘፍ 3፥1-24ትን በማንበብ ታሪኩን በአንድ አረፍተ ነገር ለማጠቃለል ሞክር።
2. በቁ 1-5 ላይ በሴቲቱና በእባብ መሃል ውይይት ሲካሄድ እናያለን። እባብ በሴቲቱ አዕምሮ ውስጥ ስለእግዚአብሄር አስተሳሰብ(Motive) ጥርጥር ለመፍጠር የተጠቀመበት ዘዴ ምን ነበረ?
3. ጠላት አዳምና ሄዋንን ያታለለው በእባብ በኩል እንደሆነ አንብበናል። ዛሬስ የእግዚአብሄርን አስተሳሰብ(Motive) እንድንጠራጠር የሚጠቀምበት መንገድ ምንድነው?
4. ያለሙታዘዛቸው የመጀመሪያው ውጤት የራቁትነት ስሜት ነበረ(ቁ 7) ለምን ይመስልሃል ራሳቸውን መሸፈን እንዳለባቸው የተሰማቸው?
5. ዛሬስ የሰው ልጆች ባዶነታቸውን ወይም እራቁትነታቸውን ለመሸፈን የሚሞክሩባቸው ነገሮች ምንድናቸው ብለህ ትገምታለህ?
6. ቁ 9-13 ሃጥያታቸውን እንዲናገሩ እግዚአብሄር አዳምንና ሄዋንን ጥያቄ ሲጠይቃቸው እናያለን። እርሱ ሁሉን የሚያውቅ ሆኖ ለምን ጥያቄ መጠየቅ አስፈለገው?
7. ከሃጥያት የተነሳ እግዚአብሄር እርግማን ሲያስተላልፍ ይታያል(ቁ 14-19)። ታዲያ ይህ እርግማን በፍጥረት ላይ ያስከተለው ነገር ምንድነው ትላለህ?
8. ቁ 15ትን ስታነብ እግዚአብሄር አምላክ ፍርድን እያስተላለፈ እንኳን ከዚያ ጋራ አብሮ መውጫ የሚሆን የሰጠው ተስፋ ምንድነው?
9. የሰው ልጅ ባለመታዘዝ እግዚአብሄርን ቢበድልም እርሱ ጸጋውን ለመስጠት እጁን ሲዘረጋ ይታያል። በቁ 21-24 ጸጋውና ምህረቱን የሚገልጸውን ሃሳብ አስረዳ።
10. እግዚአብሄር የምህረትን መንገድ ባያመቻች ህይወታችን በምን መንገድ የተለየ ይሆን ነበረ? ስለዚህስ ስጦታው ለእግዚአብሄር በሳምንቱ ውስጥ ምን ትሰጠዋለህ?

# <u>ጥናት ሰባት (ሮሜ 3፥9-31)</u>

<u>የጥናቱ ዓላማ</u>፡- እግዚአብሄር አምላክ በልጁ በየሱስ በኩል ከሃጥያታችን ነጻ በማውጣት እንዴት እንደገና ወደ ህብረት እንደመለሰን ለመማር።

<u>የጥናት መክፈቻ</u>፡- መኪና ስትነዳ አብዛኛውን ጊዜ ለመጣስ የሚፈታተንህ የትራፊክ ህግ የትኛው ነው?

1. ሮሜ 3፥9-31 ይነበብ። ጳውሎስ በተለይ በቁ 9-12 "ሁሉ" እና "አንድ ስንኳ" የሚሉትን ቃላት ሲጠቀም እናያለን። እርሱን የሚፈልግና መልካም የሚያደርገውን ሰው ሁሉ እግዚአብሄር ይቀበለዋል ለሚለው ሰው ይህ ክፍል ምን መልስ አለው ትላለህ?
2. በቁ 13-18 ውስጥ ጳውሎስ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን አንደ ጉሮሮ፥ምላስ፥ከንፈር፥ አፍ፥እግር፥አይንን ይጠቅሳል። እነዚህ ስዕላዊ መግለጫዎች ስለ መንፈሳዊና ስለ ግብረገባዊ ሁኔታችን ምን ያሳያሉ?
3. አይሁዶች የብሉይ ኪዳንን ህግ ከሃጥያት ነጻ ለመውጫ ለመጠቀም ሞክረው እንደነበረ በቁ 19-20 እናያለን። የዚህ ዓይነቱ አመለካከት ስህተቱ ምንድነው ይላል መጽሃፉ?
4. ቁ 21-31 በህግ ለመጽደቅ ላቃታቸውና ለተኮነኑ ሰዎች እግዚአብሄር ያዘጋጀውና የሰጠው ተስፋ ምን ነበረ? የሰውስ ሃላፊነት በዚህ ውስጥ ምን ነበረ?
5. በቁ 24-25 መሰረት እግዚአብሄር በክርስቶስ በኩል ለኛ የሰራውንና ያከናወነውን የሚገልጽ ቁልፍ ቃል የትኛው ይመስልሃል?
6. በነጻ ጸድቀናል(ቁ 24) ማለትም ከአሁን በኋላ ስለሃጥያት አይፈርድብንም። ጽድቃችን በአንድ በኩል ነጻ እና በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ ውድ የሚያደርገው ምንድነው?
7. በቁ 27-30 መሰረት እንዴት ነው የእግዚአብሄር ጽድቅ የሰዎችን ትምክህት ከንቱ ወይም ባዶ የሚያደርገው?
8. ይህ ክፍል እግዚአብሄር እንዴት ከውድቀታችን እንዳነሳን የሚያስተምረን ነው። ታዲያ ይህንን ክፍል ስታነብ ስለ እግዚአብሄር የሚሰማህ ስሜት ምንድነው?
9. በዚህ ምንባብ መሰረት ለማያምን ሰው ክፉውን ዜና እንዲሁም መልካሙን ዜና በምን ዓይነት ታስረዳለህ?

# ጥናት ስምንት (ሮሜ 8፥1-17)

የጥናቱ ዓላማ፡- በቅድስና ለመመላለስ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ መደገፍ እንደሚኖርባቸው ለማስገንዘብ።

የጥናት መክፈቻ፡- እንደቀልድ ለምደኸው እያደረ ለመላቀቅ የተቸገርክበት ልማድ ወይም ሱስ ሆኖብህ የሚያውቅ ነገር አለ ወይ?

1. ሮሜ 8፥1-17 ይነበብ። ሃዋርያው በቁ 1-4 ላይ ለአማኞች የሚያበስረው ታላቅ ዜና አለ። ይህ ታላቅ ዜና ምንድነው?
2. እግዚአብሄር በተኮነንበት ጊዜ በዚያ ሁኔታ ሊተወን አልፈቀደም። በቁ 1-17 መሰረት ስላሴዎች በምን ዓይነት መንገድ ነው ነጻ በመውጣታችን ተሳትፎ ያደረጉት?
3. በቁ 5-8 እንደ መንፈስ ፈቃድና እንደ ስጋ ፈቃድ በሚኖሩ ሰዎች መሃል ሃዋርያው የሚያደርገውን ማነጻጸር አስረዳ። እኛስ በየትኛው እንደተመላለስን እንዴት እናውቃለን(ቁ 9)?
4. አማኞች እንደስጋ ፈቃድ መመላለስ እንደሌለባቸው በቁ 4 ና 9 ላይ ሃዋርያው ይናገራል። ይህንን ሃሳብ ከራስህ ህይወት ልምምድ ጋራ እንዴት ታየዋለህ?
5. በጳውሎስ አነጋገር አዕምሮኣችን የሃጥያትን ኑሮ ለመኖርና የጽድቅን ኑሮ ለመኖር ያለው አስተዋጽኦ ምንድነው ይላል?
6. የጽድቅ ኑሮ መኖርን በተመለከተ ትምክህትን በመንፈስ ቅዱስ ላይ በማድረግና በራሳችን ጉልበትና ችሎታ ላይ በመታመን ያለው ልዩነት ምንድነው?
7. በቁ 10 ላይ የምታየውን በሥጋችንና በመንፈሳችን መሃል ያለውን ከፍተኛ ውጥረት በራስህ ቃላት አስረዳ። መንፈስ ቅዱስ ይህንን ውጥረት እንዴት ያረግበዋል(ቁ 11)?
8. በቁ 12-17 መሰረት ቅድስናን በተመለከተ የአማንንና የመንፈስ ቅዱስን ሃላፊነት ያሳየናል። በዚያ መሰረት የኛ ሃላፊነት ምንድነው ትላለህ? የመንፈስ ቅዱስስ?
9. ከሃጥያት እስራት ሊያላቅቅህ መንፈስ ቅዱስ በህይወትህ ለሚሰራው ሥራ በምን ዓ ይነት መንገድ ልትተባበረ የምትችል ይመስልሃል?

# <u>ጥናት ዘጠኝ (ሮሜ 8፥18-39)</u>

<u>የጥናቱ ዓላማ፦</u> የአሁኑ ዘመን መከራ ከፊታችን ካለው ታላቅ ክብር ጋራ ሲነጻጸር ምንም እንዳልሆነ ለማስተማር።

<u>የጥናት መክፈቻ፦</u> ከመቃብር በኋላ ስለሚኖረው ህይወት ስታስብ ቶሎ ብሎ የሚታይህ ነገር ምንድነው?

1. ሮሜ 8፥18-39 ይነበብ። በዚህ ክፍል በቁ 18-25 መሰረት የሰው ልጆችም ሆኑ ፍጥረት በሙሉ እያለፈበት ስላለው የአሁን ዘመን መከራ ጸሐፊው ምን ይላል?
2. <u>በነዚሁ</u> ቁጥሮች ውስጥ ጸሐፊው በመከራ ውስጥ ስለሚኖረን ተስፋ ምን ያስተምረናል? ይህስ ተስፋ በመከራ ውስጥ ስትሆን ለአንተ በግልህ ምንያህል መጽናናት ይሆንሃል?
3. በቁ 19 ላይ ሃዋርያው በናፍቆትና በጉጉት እንድንጠብቅ በቁ 25 ደግሞ በትዕግስት እንድንጠብቅ ይነግረናል። እነዚህ ሁለት ሃሳቦች እንዴት ይስማሙልሃል?
4. በቁ 26-27 መሰረት መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን በምናልፍባቸው መከራ፥ ጭንቀትና ድካም እንዴት ነው የሚያግዘን?
5. ቁ 28-39ን በማንበብ እግዚአብሄር ለእኛ ስላለው ዓላማ ምን ትረዳለህ? ይህንንስ አላማ ከግብ ለማድረስ ምን ዓይነት እርምጃዎችን ወስዷል?
6. ቁ 28ትን ሰዎች በተለያዩ ሁኔታዎች ሲጠቅሱት ይሰማል። አንተስ ስለዚህ ጥቅስ ያለህ መረዳት ምንድነው?
7. የእግዚአብሄር በህይወታችን የሚያልፉትን ነገሮች ሁሉ ማወቅና መቆጣጠር በህይወትህ ላለፍክባቸው አመቺ ያልሆኑ ሁኔታዎች ረድቶህ ያውቃል ወይ?
8. ቁ 31-34ትን በማንበብ እግዚአብሄር የገባልንን ቃልኪዳን እንደሚፈጽመው ምን ማረጋገጫ እንዳለን ታያለህ?
9. በህይወታችን አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደሚገጥሙን ቁ35-39 ያሳየናል። በህይወትህ የመጡ ችግሮች የእግዚአብሄርን ፍቅር እንድትጠራጠር ያደረጉበት ጊዜ አለ ወይ?
10. በህይወታችን የሚመጡ ከባድና ሃይለኛ ጠላቶች የሚመስሉን ነገሮች እንዲያውም በበለጠ የአምላካችንን ፍቅር ጠንካራነትና ሃይለኛነት በምን ዓይነት የሚያረጋግጡልን ይመስልሃል?
11. በዚህ ሳምንት እስከዛሬ አጥብቆ በመያዝ ወደፊትም ለሚይዘን ታላቅ ፍቅሩ እግዚአብሄርን ለማመስገን ጊዜ ውሰድ።

# <u>ጥናት አስር (ሐዋ ሥራ 2፥1-47)</u>

<u>የጥናቱ ዓላማ፡-</u> በቤተክርስትያን ተልዕኮና የቅዱሳን ሕብረት ተሳትፎ ማድረግ አስፈላጊነቱን ለማስገንዘብ።

<u>የጥናት መክፈቻ፡-</u> ቤተክርስትያን ልብን ከማሳረፍ ይልቅ ልብን የሚሰብር ቦታ እንደሆነች ተሰምቶህ ያውቃል ወይ?

1. ሃዋ ሥራ 2፥1-47 ያለውን ክፍል በማንበብ በዚያ ሥፍራ የተካሄደው ነገር በምን መንገድ በ 1፥8 ኢየሱስ የገባውን የተስፋ ቃል የፈጸመ ይመስልሃል?
2. በቁ 14-21 ጴጥሮስ እንዴት ነው የኢዩኤልን ትንቢት በመጥቀስ የሆነውን ነገር የሚገልጸው?
3. ቁጥር 36ትን መስበክ የቤተክርስትያን ተልዕኮ ነው። በዚህ ቁጥር መሰረት ጴጥሮስ ይህንን ስብከት መቀበል ያለባችሁ ለምንድነው ይላቸዋል?
4. የቀድሞዋ ቤተክርስትያን ስብከትና በአሁን ጊዜ ካለችው ቤተክርስትያን ስብከት ጋራ ስታነጻጽረው እንዴት ታየዋለህ?
5. ከቁ 22-39 ስናነብ ብዙዎች እንደተለወጡ እናያለን። ለምን ይመስልሃል ስብከቱ የብዙዎችን ልብ መንካት የቻለው?
6. በቁ 42-47 አንድ ተልዕኮና አንድ አይነት መልዕክት የነበራቸው በአንድነት ሕብረት እንደጀመሩ ይታያል። በዚህ ሕብረት ውስጥ ምን ትመለከታለህ?
7. በመቅደስም በቤታቸውም በብዛትና በአነስተኛ ቁጥር ይገናኙ እንደነበረ ቁ 46 ያሳየናል። ለምን ይመስልሃል እነዚህ ሁለቱም አስፈላጊ የሚሆኑት?
8. በቁ 47 መሰረት ለቤተክርስትያን እድገት የኛ ድርሻ የእግዚአብሄርስ ድርሻ ምን እንደሆነ ታያለህ?
9. ለቤተክርስትያን እድገት የእግዚአብሄር ድርሻ እንዲሁም የሰው ድርሻ መኖሩን ማየት አለመቻል የሚያስከትለው ችግር ምን ይመስልሃል?
10. ቤተክርስትያናችን አሁን ከተመለከትነው ከጥንቷ ቤተክርስትያን የወንጌል ሥርጭት ልምድ ምን ትምህርት መቅሰም ትችላለች ትላለህ?

# ጥናት አስራ አንድ (ኤፌ 4፥1-16)

<u>የጥናቱ ዓላማ፡-</u> አንዱ የሌላውን ሥጦታ በማክበር እርስ በእርስ የመተናነጽ ሃሳብ በቤተክርስትያን ውስጥ እንዲጠነክር ለመርዳት።

<u>የጥናት መክፈቻ፡-</u> ቤተክርስትያንን የከፈሉ የሰማሃቸው ወይም ያየሃቸው ነገሮች አሉ ወይ?

1. ኤፌ 4፥16 በማንበብ በቁጥር 1-3 የተጠቀሱት ባሕርዮች ለቤተክርስትያን አንድነት አስፈላጊ የሆኑበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?
2. ክርስትያኖችን አንድ የሚያደርጉ ነገሮች እንዳሉ የታወቀ ነው። በቁጥር 4-6 ላይ ጳውሎስ የጋራ እምነቶች በማለት የሚጠቅሳቸው የአንድነት መሰረቶች ምንድናቸው?
3. የአማኞችን ሕብረትና አንድነት ለማጠናከር በግልህ ምን አይነት እርምጃዎችን መውሰድ ትችላለህ?
4. ነገስታት በጦርነት ድል ሲያደርጉ ስጦታ መስጠት የተለመደ ነው። ክርስቶስ ድል ሲያደርግ የሰጠው ስጦታ ምንድነው? ቁጥር 7-11
5. በእነዚህ ቁጥሮች የተጠቀሱት ስጦታዎች የመሰጠታቸው ዋና ዓላማ ምንድነው ይላል?
6. እግዚአብሄር ለእያንዳንዱ አማን ስጦታን ሰጥቷል። አንተ በአካሉ ውስጥ ሊኖርህ ለሚገባው አገልግሎት እግዚአብሄር በምን ሥጦታ ያስታጠቀህ ይመስልሃል?
7. ያልበሰለችና ጨቅላ የሆነችን ቤተክርስትያንን የሚያሰጋት አደገኛ ነገር በቁጥር 14-16 መሰረት ምን ይመስልሃል?
8. በየዘመኑ የትምህርት ነፋስ አለ። በዚህ በኛ ዘመን ቤተክርስትያንን የገጠማት የትምህርት ነፋስ ምንድነው ትላለህ?
9. ቤተክርስትያን ጤነኛ እድገት እንዲኖራት ካስፈለገ እውነት በፍቅር መነገር ይኖርበታል። የእውነት በፍቅር ያለመነገር የሚያስከትለው አደጋ ምን ይመስልሃል? በሌላ በኩል ደግሞ ፍቅርስ ያለእውነት መነገሩ የሚያስከትለው ችግር ምንድነው?
10. ጳውሎስ ቤተክርስትያንን በአካል ይመስላታል። አንተ በዚህ አካል ውስጥ የትኛውን ብልት ነው የምትሞላው? እውነትን በፍቅር የመናገር ሃላፊነትህንስ እየተወጣህ ይመስልሃል ወይ?

# ጥናት አስራ ሁለት (2ኛ ጴጥ 3፥3-14)

<u>የጥናቱ ዓላማ፡-</u> የጌታ የየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጻት በጉጉት መጠበቅ ለኑሮአችን ተስፋና ብርታት ሊሆነን እንደሚገባ ለመማር።

<u>የጥናት መክፈቻ፡-</u> የጌታን መምጣት ስታስብ ከሚያጓጉህ ነገሮች ዋነኛው ምንድነው?

1. 2ኛ ጴጥ 3፥3-14 ስናነብ አማኞች በመጨረሻ ዘመን በጌታ ምጻት የሚያሾፉ ሰዎች እንደሚገጥማቸው ያረጋግጣል። የማሾፌይ ምክንያታቸው በቁ 3-4 መሰረት ምንድነው?
2. እለት እለት የዚህ ዓይነት አመለካከት ካላቸው ሰዎች ጋራ የመዋልና የሚያሾፉትን መስማት በክርስትና ህይወት ምን የሚያስከትል ይመስልሃል?
3. በውሃ ምድርን እንዳጠፋ ማስታወስ ክርስትያን ስለጌታ ምፃት ያለውን እምነት እንዴት ያጠናክራል?
4. የእግዚአብሄር ዘመን አቆጣጠር በሰዎች ውስጥ የሚፈጥረው ፍራስትሬሽን ወይም ቤነፊት (ጥቅም) ምንድነው ትላለህ?
5. ጴጥሮስ በቁ 10 ላይ የጌታ ቀን እንደ ሌባ ይመጣል ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
6. ጌታ በምስጢር ከዚህ በፊት መጥቷል ብለው ለሚያስተምሩ ሰዎች ይህ የጴጥሮስ ትምህርት ምን የሚያስተምረው ወይም የሚነግረው ነገር አለ?
7. ስለሚመጣው ፍርድ ቁ 7 ና 10 ምን ሃሳብ ይሰጠናል?
8. በቁ 10-13 መሰረት እግዚአብሄር አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን ይፈጥራል። አሁን በምድር ያለው ህይወት ወደፊት ከሚመጣው ጋራ ሲነጻጸር ምንይመስል ይመስልሃል?
9. የጌታን ምጻት እለት እለት እያሰቡ መኖር በአኗኗራችንና በአመለካከታችን ሊያመጣ የሚችለው ለውጥ ምንድነው ትላለህ?